# Learning by Ear 2013

# መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ - ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE THREE: አስቸጋሪ ጅማሬ

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ዳንኤል AND ንጉሴ MEET IN THE CLASSROOM**

- **ዳንኤል (M, 16)**
- **ንጉሴ (M, 16)**
- **ርዕሰ መምህር ት ሰብለ (F, 50)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ትዕግስት (F, 15)**
- **እየሩስ (F, 15)**
- **NOISY STUDENTS (F/M, 15/16)**

**SCENE 2: ሙላቱ AT ርዕሰ መምህርት ሰብለ OFFICE.**

- **ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)**
- **ሙላቱ (M, 45)**

**SCENE 3: ምህረት AND ርዕሰ መምህርት ሰብለ SHOP IN TOWN**

- **ምህረት (F, 15)**

- ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)

**SCENE 4: ንጉሴ AND ጃለታ DRIVE BACK HOME FROM SCHOOL**

- ጃለታ (M, 45)
- ንጉሴ (M, 16)

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ በየዕለቱ ከባድ ውሳኔዎችን መወሰን ስላለባቸዉ ስለ ሶስት ተማሪዎች ጉዳይ የምናቀርበዉ ተከታታይ ድራማ ክፍል ሶስት ነዉ። እስኪ ዛሬ ምህረት፣ ዳንኤል እና ንጉሴን በአዲሱ ትምህርት ቤታቸው ከማግኘታችን በፊት እስከ አሁን ምን እንደተከሰተ ጠቅለል አድርገን እናስታዉስ፤

ምህረት፣ ለአባቷ፣ ለአቶ ሙላቱ፣ የት እንደምትሄድ ሳትነግረው ሹልክ ብላ ወደ ትምህርት ቤቷ ሄዳ ነበር። ወደ ትምህርት ቤቱ ለመግባት ደግሞ የትምህርት ቤቱ ጥበቃ ጓድ እንኳ አላገዳትም ነበር ።

2. **GUARD (EP02, LINE 28):** “ሃይ! አንቺ! አንቺ ሴት! ቁሚ! (…) ያቺን ልጅ አስቁሙልኝ! ያዟት!”

በቦንጎ አካዳሚ ችግሯን ለርዕሰ መምህር ሰብለ ተናገረች።

3. **ምህረት (EP 02, 54):** “ እውነቴን ነው፣ ሁሉም ነገር እውነት ነው፤ እትዬ ሰብለ። አባቴ ወደ ቦንጎ አካዳሚ መጥቼ ከሚያየኝ ይልቅ ቢድረኝ ይመርጣል! ”

ርዕሰ መምህርቷ ደንግጠዋል ግን የተናገረችውን አምነዋታል።

4. **ሰብለ <u>(EP 02, 55):</u>** “እሺ፣ ምህረት። ለአንቺ የተለየ ነገር አደርጋለሁ (…) የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ ባይኖርሽም ትምህርት መጀመር ትችያለሽ።”

5. SFX: school bell

ዛሬ ይዘን የቀረብነዉ ሶስተኛው ክፍል የድራማ ርዕስ “አስቸጋሪ ጅማሬ” ይሰኛል። እለቱ በቦንጎ አካዳሚ የመንፈቅ ዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ስለሆነ ተማሪዎች ንጽህና ጥሩ ሆኖ በተዘጋጀላቸዉ አዲሱ ክፍላቸው ውስጥ አስተማሪያቸውን እየተቁነጠነጡ በመጠበቅ ላይ ናቸው። ምህረት እስከ አሁን ክፍሏ አልደረሰችም፤ ዳንኤል እና ንጉሴ ግን ወንበራቸው ላይ ቁጭ ብለዋል። የክፍሉ ድባብ በጭንቀት የተሞላ ይመስላል...

## SCENE 1: ዳንኤል AND ንጉሴ MEET IN THE CLASSROOM

6. SFX: CLASSROOM ATMO

7. **ዳንኤል:** (addressing class) ሰላም ሰላም፣ ሁላችሁም!! ሁላችንም ለክፍሉ አዲስ እንደመሆናችን እራሴን በይፋ ማስተዋወቅ እፈልጋለሁ። (starts clapping a rhythm) ይኸው እንግዲህ ጀመርን! (sort of rap or rhyme poetry) የሚባለው ስሜ ዳን። ያይደለሁ ካንተ ወገን! እቅድ አለኝ የምትል፣ ተነሳ ተናገር ለዳን። እችላለሁ ብለህ ካመንክ፤ እኔ ነኝ ሰውዬክ። እቅድ ከሌለህ ግን ሂድ መጥበሻ ላይ ተንጨርጨር። በላ አድናቂዬ ከሆንክ፣ አንዴ አድርገው ሞቅ ሞቅ!

8. SFX: WILD APPLAUSE FROM STUDENTS ESPECIALLY GIRLS

9. **ንጉሴ:** (refusing) ተው ባክህ! ፈጽሞ፣ አይሆንም፣ ስማ ስማ ዳንኤል፣ እኔ የአንተ አድናቂ አይደለሁም። በዚህ ለዛ በሌለው ቅላፄህ እና መጥፎ ባህሪህ የማይሆን ነው። ስሙ ሰዎች፤ (same rap or rhyme poetry) ስሜ ንጉሴ፣ በትንሽ ውስዋሴ፣ ሸዋጅ ነኝ ነፍሴ፣ ቀልድ አይምሰላችሁ ንጉሴ፣ ቀዉጢ፤ ቀዉጢ፤ የገባው ፍሪኪ!

10. SFX: MORE WILD APPLAUSES FROM CLASS ESPECIALLY GIRLS

11. ዳንኤል፡ “ዋው፣ ምን አይነት አስቂኝ ግጥም ነው!”

12. SFX: FOOTSTEPS IN HIGH HEELS. ሰብለ WALKS IN WITH ምህረት

13. ርዕሰ መምህርት ሰብለ፡ (ironically) ደህና፣ እንዴታ ያለ አስደሳች ሰላምታ ነው ባካችሁ ይሄ ለእኔ ለርዕሰ መምህርቷ. (serious) በሉ አሁን ይበቃል! ጸጥታ፣ ሁላችሁም ጸጥታ!

**PIN DROP SILENCE**

14. ሰብለ፡ አዎ እንዲህ ይሻላል። አሁን ለክፍላችን አዲስ የሆነች ሌላ ተማሪ አስተዋውቃችኋለሁ። እሺ,,,,ሁላችሁም ምህረት ሙላቱን ተዋወቋት፣

15. SFX: BEWILDERMENT AND SHOCKED REACTION FROM STUDENTS

16. ሰብለ፡ አዎ፣ አውቃለሁ፣ የትምህርት ቤታችንን የደንብ ልብስ አለበሰችም። ያ ግን ማንኛችሁንም ሊያስጨንቃችሁ አይገባም። ሁላችሁም የገዛ ቤቷ የመጣች ያህል እንዲሰማት አድርጋችሁ በጥሩ እንድትቀበሏት እፈልጋለሁ። (To ምህረት) ምህረት፣ ሂጂና ተቀመጪ።. (To ንጉሴ) አንተ ስምህ ማን ነው?

17. ንጉሴ፡ (politely) ስሜ ንጉሴ ነው። ንጉሴ ጃለታ፤ መምህርት.

18. ሰብለ፡ (strict voice) ንጉሴ ጃለታ፣ ከአሁን ጀምሮ የክፍሉ አለቃ ነህ። ማንም ሰው ቢረብሽ፣ ወይም የትምህርት ቤቱን ሕግ ቢጥስ ስማቸውንጽፈህ በቀጥታ እንድታመጣልኝ እፈልጋለሁ። በእዚህ በቦንጎ አካዳሚ መመሪያችን፣ “ጠንክሮ መስራት፣ መልካም እድል ያስገኛል” የሚል ነው እና ሁላችሁም እዚህ የሚጠብቃችሁ ይህ ነው። አሁን መጽሐፍታችሁን ክፈቱ እና የመጀመሪያ ቀናችሁን በትምህርት ቤታችን ተደሰቱበት። የሂሳብ መምህራችሁም ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ይመጣል።

19. **SFX: HIGH HEELED SHOES WALKING AWAY**

20. **SFX: DOOR CLOSED**

21. **ምህረት:** (timidly) ይቅርታ እዚህ አጠገብሽ መቀመጥ እችላለሁ?

22. **እየሩስ:** (sarcastically) ልጅት፤ ይልቅ እራስሽን ይቅርታ ጠይቂ! እ,,,, ይቅርታ፣ ግን አይሆንም። ቦታው ተይዟል።

23. **SFX: STUDENTS ARE STARTLED BY እየሩስ'S RESPONSE**

24. **ንጉሴ:** ሃይ፣ ሄይ! የእዚህ ክፍል አለቃ እኔ ነኝ። ይህቺ ልጅ,,,እ,,ምህረት ነዉ. ስምሽ አይደል? ልክ ነኝ? እዛ ከአንቺ አጠገብ እየሩስ,,,እዛ ትቀመጣለች ፡ ቦታዉ ባዶ ነው። ካልተመቸሽ አንቺ ሂጂ!

25. **እየሩስ:** ጥሩ ሀሳብ፣ አቶ ፖሊስ። ለማንኛውም እኔ ሌላ ቦታ ሄጄ ብቀመጥ እመርጣለሁ።

26. **ምህረት:** አዝናለሁ- እኔ ላበሳጭሽ ፈልጌ አይደለም።

27. **እየሩስ:** ተበሳጨሁ ያለ አለ? ስታይኝ በእንዳንንቺ አይነቷ የምበሳጭ እመስላለሁ? ለአንዲት ቆሻሻ፣ ደባደቦ ለባሽ፣ ቅርናታም፣ በባዶ እግሯ ለምትሄድ ልጅ? አይምሰልሽ... አትመጥኝኝም፣ ደረጃዬ አይደለሽም እሺ! እኔ እኮ ያን ሁሉ የነጻ ትምህርት እድል ወጪ. ለምን ለእንዳንቺ አይነቱ ሰው እንደሚያባክኑ አይገባኝም። የሚያደርጉት ሁሉ የዚህን ትምህርት ቤት መልካም ስም መበከል ነው። ጥሩ፣ መቀመጥ ትችያለሽ፣ ተቀመጭ። አንቺ ጠንቋይ፣ ተጎለቺበት!

28. **SFX: STUDENTS REACT WITH SHOCK**

29. **SFX: እየሩስ GRABS HER STUFF**

30. **TRUDY:** ዝም በይያት አሏን! ነይ ከእኔ ጋር መቀመጥ ትችያለሽ። ትዕግስት አባላለሁ።

31. **MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 2: ሙላቱ AT ርዕሰ መምህርት ሰብለ OFFICE**

32. **SFX: OFFICE ATMO**

33. **SFX: HIGH-HEELED FOOTSTEPS ENTERING**

34. **ርዕሰ መምህርት ሰብለ:** ይቅርታ የምህረት አባት አቆየሆት። ልጅዎን ከክፍል ጓደኞቿ ጋር ማስተዋወቅ ነበረብኝ።

35. **ሙላቱ:** **(confused)** እንደ እኔ ምኑም አልጨበጥልህ ነው ያለኝ! አቅማችን እዚህ ትምህርት ቤት ልናስተምራት አይፈቅድልንም። ክፍያዉን አንችለዉም። ልጄ እዚህ መግባት አይገባትም። ምንአልባትም ይሄኔ አሁን ተማሪዎቹ እየሳቁባት ነው።

36. **SFX: ሰብለ SITS DOWN**

37. **ሰብለ:** አቶ ሙላቱ ላለፉት 20 አመታት አስተማሪ ነበርኩ። ታድያ በዚህ ሁሉ ዘመኔ እንደ እርሶ ልጅ ለመማር ቆርጦ የተነሳ ሰው አላጋጠመኝም። እኔ ቢሮ ደርሶ ለመግባት ጥበቃውን አምልጣ ሮጣ እንደመጣች ያዉቃሉ?

38. **ሙላቱ:** ምህረት ምን አደረገች ነዉ የሚሉኝ?

39. **ሰብለ:** ግዴለም ምንም አይጨነቁ። ያ ከነጥቡ ውጪ ነው። እያልኩ ያለሁት የመማሩን እድል እንስጣት ነው። መማር ይገባታል። በእግዚር ፈቃድ እድሉን አግኝታለች። በእርግጠኝነት መቼም ይህን የመሰለ ችሎታዋ የሆነ ሰው ማዕድ ቤት ውስጥ እንዲባክን እርሶም አይፈልጉም!

40. **ሙሉቱ:** የሚያስፈልጓት ነገሮችስ? የትምህርት ቤት የደንብ ልብሶች? ጫማዎች – (stresses) ጫማዎች - እንዳውም ቦንጎ አካዳሚ የመከረው ቆዳ ጫማ ነው ! እና

41. **ሰብለ:** ስለዚህ አይጨነቁ። እነዚህን ሁሉ ወጪዎች እኔ በግሌ እሸፍናለሁ። እንደነገርኮዎ ልጅዎ የራባት አውቀት ነዉ። እኛ ደግሞ እዚህ ያለነዉ ያንን ልንመግባት ነው።

42. **ሙሉቱ:** ስለዚህ፣ የሚሉኝ ስለ ወጪው አትጨነቅ ነው።

43. **ሰብለ:** እያልኩ ያለሁት፤ ምህረትን እንድትማር ይፍቀዱላት ነዉ። አግዟት። ጥሩ ትምህርት ካገኘች በኋላ ወደፊት ምን እንደምትሆን አያውቁም።

44. **ሙሉቱ:** (takes time to think) ህምምም...መልካም...ይሁን - ላስብበት።

45. **ሰብለ:** የሚያስቡበት ጊዜ የለንም። ምህረት ክፍል ገብታለች። ወይ መቆየት አለባት አለበለዚያ አሁኑኑ ይዘዋት ይሂዱ። ምርጫው የእርሶ ነው። እኔ የበኩሌን ተናግሬያለሁ።

46. **ሙሉቱ:** (takes deep breath) ጥሩ፣ እንግድያዉ ይተዋት ትቀጥል። ቢያንስ ለአሁን። ሌሎች ልጆች በልብሶቿ ወይም በቤተሰቧ ምክንያት ካበሳጯት ግን ወዲያውኑ ከትምህርት ቤት አስወጣታለሁ።

**KW BEGIN**

47. **ሰብለ:** እዚህ ከምስኪን ቤተሰብ የመጣችው ምህረት ብቻ አይደለችም። ጥቂት ቢሆኑም የትምህርት እድል አግኝተው የተቀበልናቸው አሉ። እንደውም ለዚህ እድል በመብቃቷ ሊኮሩባት ይገባል። አንድ ተማሪ የፕሪዚዳንታዊ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት እጅግ በጣም ጎበዝ መሆን አለበት። ይህ ትልቅ ክብር እና እድልም ነው።

48. **ሙላቱ :** (grumbles) ጥሩ፤ ታዲያ ፕሬዚዳንቱ እንዲህ ሩህሩህ እና ለጋስ ከሆኑ ከድህነት መውጫ የሚሆን ፕሬዝደንታዊ የገንዘብ ድጋፍ ለምን አይፈጥሩም? , ,ለማንኛዉም ያን ይርሱት እእእ ሀ፣ እሺ፡፡ አሁን ስራ አለመግባቴን ማሳወቅ አለብኝ፡፡

49. **ሰብለ:** እሺ እሺ ብዙ አላስቆዮትም፡፡ ስለ ጊዜዎ አመሰግናለሁ፡፡ በትምህርት ቤት ዉስጥ ልጅዎ እንዴት እንደሆነች ሁኔታዉን አይተን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እናሳውቆታለን፡፡

**KW END**

50. **ሰብለ:** ግን ይህንን ካላልዎት በኋላ ላይ ምህረትን ወደ ከተማ ወስጄ የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ ትለካለች፡፡ ጫማም እገዛላታለሁ፡፡

51. **ሙላቱ :** እውነትዎን ነው? ጊዜ አይባክንቦትም አይደል? (jokingly) ከእናንተ ጋር ብመጣስ ለእኔም የሆነ ነገር ይገዙልኛል?

52. **ሰብለ :** (confused) ኧ...ይቅርታ? የምርዎን ነው?

53. **ሙላቱ :** (laughs sheepishly) ለቀልድ ያህል ነው እመቤቴ፡፡

54. **ሰብለ :** (firmly) ይቅርታ አቶ ሙላቱ፡፡ እንዲህ አይነት ቀልዶች አይመቹኝም፡፡ ቅር ካላሎ አሁን ቢወጡ ይሻላል!በመምጣትዎ አመሰግናለሁ፡፡

55. **MUSIC INTERLUDE**

## <u>SCENE 3: ምህረት AND ርሰስ መምህርት ሰብለ SHOP IN TOWN</u>

56. **SFX: STREET ATMO**

57. **SFX: FOOTSTEPS - ምህረት AND ሰብለ ARRIVING**

58. **ሰብለ**: ይኸው እንግዲህ ደርሰናል። የትምህርት ቤት የደንብ ልብሱ የሚሰፋበት መደብር ያውልሽ እዝያ ጥጉ ጋራ ።

59. **ምህረት**: መምህርት በእውነት በጣም ደስ ብሎኛል። እንዴት ውለታዎን እንደምከፍል አላውቅም።

60. **ሰብለ**: ትምህርትሽ ላይ ትኩረት በማድረግ ልትክሺኝ ትችያለሽ። ከአንቺ የምፈልገው ይህንን ብቻ ነው። ታውቂያለሽ ምህረት፤ ትምህርት ለመማር ሳደርግ የነበረዉን ከፍተኛ ጥረት እንዴት እንደነበር ታስታውሽኛለሽ...ለመማር ያላደረኩት ጥረት የለም።

61. **ምህረት**: እውነትዎን ነው?

62. **ሰብለ**: አዎ! ያን ያህል ጊዜዉ እጅግ የቆየ ቢሆንም ምን እንደሚሰማሽ አውቃለሁ። አየሽ ሴት ልጅ በመሆኔ ብቻ ወላጆቼ ትምህርት ቤት እንድገባ አይፈልጉም ነበር። መማር የምፈልገዉን ነገር ሁሉ ማግኘት የምችለዉ ወይም መማር ያለብኝ ከእናቴ ብቻ ነዉ ብለዉ ያስቡ ነበር። አክስቴ ግን መማር እንዳለብኝ ቆርጣ ትምህርት ቤት ላከችኝ። ለዚያም ነው ማንኛውንም ልጅ የመማር መብት መንፈግ እንደሌለብኝ ለራሴ ቃል የገባሁት።

63. **ምህረት**... ይገርማል እኔይህን አላውቅም ነበር...

**KW BEGIN**

64. **ሰብለ**: እና፣ ንገሪኝ። በቦንጎ አካዳሚ የመጀመሪያው ቀን ውሎሽ እንዴት ነበር? ተመቸሽ?

65. **ምህረት :** (pretending) አስደሳች ነው! ወድጄዋለሁ፡፡ የክፍል ጓደኞቼ ሁሉ ትሁት እና ተግባቢዎች ናቸው እንዳውም ትግስት የምትባል ጓደኛ አግኝቻለሁ፡፡ አጠገቧ ነው የምቀመጠዉ፡፡ ለእኔ ተመችታኛለች፡፡

66. **ሰብለ :** ምህረት፣ ይህን የምትዪኝእጅግ ትህትናን ለመላበስ ብለሽ ነው፡፡ በጣም አስቸጋሪና ከባድ ቀን እንደገጠመሽ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ለአዲስ ተማሪ የመጀመሪያ የትምህርት ቤት ዉሎ መቼም እንዲህ ቀላል ሆኖ አያውቅም። በተለይ ደግሞ አብዛኛዎቹ ተማሪዎቻችን በጣም ሀብታም ከሆኑ ቤተሰቦች የመጡ በመሆናቸው ለእንዳንቺ አይነቱ ልጅ ይከብዳል፡፡ ግን ያ ሊረብሽሽ አይገባም፡፡ የስራ ባልደረቦቼ ተማሪው በአጠቃላይ እንዳይሰማው፣ ተመችቶት እንዲማር የቻሉትን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡

67. **ምህረት :** በእውነት ምቾት ነው የተሰማኝ ፡፡

68. **ሰብለ :** ጥሩ፡፡ ቦንጎ የሚፈልገው ያንን ነው፡፡ ወደኛ የሚመጣውን ሁሉ በደስታ እንቀበላለን፤ ለሁሉም ሰዉ ጥሩ ጓደኛም እንሆናለን፡፡ ማንም ሰው በድህነትሽ ምክንያት ቢሰድብሽ ስለዚያ ሰው ልታሳዉቂን ይገባል፡፡ እሺ? አሁን እንሂድ!

**KW END**

69. **SFX: SHOP DOOR OPENED AND CLOSED, BELL RINGS**

70. **ሰብለ :** እሺ, , ,በዪ እስኪ አሁን የደንብ ልብስሽን እንምረጥ…ተመልከቺ! እዛ ጋር ያለው ! ምን ይመስልሻል?

71. **SFX: HANGER REMOVED FROM THE RACK**

72. **SFX: CLOTH RUSTLING**

73. **ምህረት፡** (excited) ወይኔ! የቦንጎ አካዳሚ የደንብ ልብሶች! እኔ አሁንም ህልም ነው የሆነብኝ። የቦንጎ አካዳሚ ትምህርት ቤት ተማሪ መሆን በጣም ነው የምፈልገው,,,,፣

74. **ሰብለ፡** (proudly) አንቺማ አንዱ መሆን ይገባሻል፣ ምህረት። ሂጅና «ዩኒፎርሙን» ለኪ።

75. **MUSIC INTERLUDE**

## <u>SCENE 4: ንጉሴ AND ጃለታ DRIVING BACK HOME FROM SCHOOL</u>

76. **SFX: CAR DRIVING IN A BUSY STREET, CAR RADIO ON**

77. **ጃለታ፡** ንጉሴ፣ ከትምህርት ቤት ከወጣን ጀምሮ አንድ ቃል አልተነፈስክም።በል እስኪ ለእዚህ ሽማግሌህ በቦንጎ የመጀመሪያ ቀንህ እንዴት እንደነበር ንገረው።ለመስማት ጓጉቻለሁ።

78. **ንጉሴ፡** (disinterested) ምንድን ነውማወቅ የምትፈልገው አባዬ?

79. **ጃለታ፡** ሁሉንም ነገር! ስለ ትምህርት ቤቱ? ስለ ክፍል ጓደኞችህ? ስለ አስተማሪዎችህ? ማለቴ ይህ ለአንተ አዲስ የህይወት ጅማሬ ነው፣ አይደለም እንዴ?

80. **ንጉሴ፡** ርዕሰ መምህርትዋ የክፍል አለቃ አደረጉኝ።

81. **ጃለታ፡** (very excited) እውነትክን ነዉ? ንጉሴ ደስ ይላል ባክህ! በመጀመሪያው ክፍል በገባህበት እለት ሰዎችን መማረክ ጀምረሀላ። እንዲህ ነው የእኔ ልጅ! በአንተ ደስ ብሎኛል። እናትህ ይህንን ስትሰማ እንደምትፈነድቅ እርግጠኛ ነኝ።

82. **ንጉሴ፡** እኔም እርግጠኛ ነኝ።

83. **ጃለታ፡** (concerned) ግን ንጉሴ የተደሰትክ አትመስልም፡፡ የክፍል አለቃ መሆን አልፈለክም ነበር እንዴ?

84. **ንጉሴ፡** አልፈለኩም፡፡ ማለቴ አይደለም፡፡ የክፍል አለቃ ስለመሆን አይደለም፡፡

85. **ጃለታ፡** እሺ፣ ታድያ ...ሌላ ነገር አለ? እንዴት ነው እዚያ የምንወድደው ትኩስ ምግብ የሚገንበት ቤት ጎራ እንድንል ፈልገሀል እንዴ? እንዲያውም እዚያ ከደረስን በኋላ ቁጭ ብለንታጫውተኛለሀ፡፡

86. **ንጉሴ፡** አይ፣ አያስፈልገንምአባ! ይሄ ዳንኤል የሚባለው ልጅ እኮ ነው፡፡

87. **ጃለታ፡** አሀ...ዳንኤል, , , ቀጥል...ምን አደረገ?

**KW BEGIN**

88. **ንጉሴ፡** የሆነ ምናምን...

89. **ጃለታ፡** ምን?

**90. SFX: CAR COMES TO SUDDEN HALT BUT ENGINE STILL RUNNING**

91. **ጃለታ፡** እሺ፣ አሁን የበለጠ ለመስማት ጓጉቼያለሁ፡፡ የቀውጢንጉሴን ስሜት ለማበላሸት ይሄ ዳንኤል ምን አደረገ ነዉ የምትለኝ?

92. **ንጉሴ፡** (angry) አባዬ! እንደዛ እያልክ አትጥራኝ ብዬሃለሁ! ስሜ አጭር እና ግልጽ ነው፤ ንጉሴ፡፡

93. **ጃለታ፡** አሃ, , ,፣ ምን ሆነሀል? አባትሀ እኮ ነኝ፡፡ ሁሉን ነገር ልታማክረኝ እና ልትነግረኝ ትችላለሀ እኮ፡፡ ችግርህን ሁሉ ለመፍታት ቃል እገባልሀለሁ! ንገረኝ! ዳንኤል፤ አንተን ለማናደድ ምን እንዳደረገ ንገረኝ?

94. **ንጉሴ፡** አሁን ወደ ቤት እንሂድ! በቃ እርሳው አባዬ፡፡

95. **ጃለታ**: ንጉሴ፣ ሁልጊዜም ምንም ሳንደባበቅ በግልጽ እንነጋገራለን፡፡ ደግሞ ታዉቃለህ ምን ያህል እንደምጨነቅልህ፣ እንዴት...

**KW END**

96. **ንጉሴ :** (not touched) አባዬ... ስለዚህ ጉዳይ ፈጽሞ ባናወራ እመርጣለሁ፡፡ እሺ? እባክህ፣ ዝም ብለን እንሂድ !

**97. SFX: CAR DRIVES AWAY IN A HURRY**

**98. <u>OUTRO - NARRATOR:</u>**

ንጉሴ እየተረበሸ ቢሆንም ስለረበሸው ነገር ለአባቱ መንገር አልፈለገም፡፡ የሚያስበዉ ከሰዉ ጋር እንዳልተግባባ ብቻ ነዉ፡፡ ግን እንዴት ይቋቋመዉ ይሆን? ዳንኤል በበኩሉ በእርሱ እና በንጉሴ መሀከል ፉክክሩ እንደተጀመረ ስለተሰማው ቤት እንደደረሰ ለጓደኞቹ በቪዲዮ ዘገባው ቁጣውን ሊያስተላልፍላቸው ወስኗል፡፡

እናንተም አድማጮች ስለዝግጅቶቻችን dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ-ገጻችን አልያም የፌስቡክ አድራሻችንን በመጎብኘት የበለጠ መረዳት ትችላላችሁ። በዚሁ እስከሚቀጥለዉ ዝግጅት እያልን እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።